# የ2018 የአመቱ ሁለት ምርጥ ኢትዮጵያውያን
# ዮሴፍ ገብሬ (ጆሲ- ኢን ዘ ሃውስ) እና የዙሪክ ስዊዘርላንድ ኢትዮጵያውያን እስፖርት ፌደረሽን
# በኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ የተመረጡ
# (ጌታቸው ረዳ)




ዮሴፍ ገብሬ (ጆሲ) ህመምተኛውና የተቸገረው የኮ/ል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ከአገር መውጣት መንግሥታዊ መግለጫን በራዲዮን ያነበበው ታሪክ የማይረሳው እወቁ ጋዜጠኛ ዳርዮስ ሙዲ Journalist Darios



Tedros Teklegiorgis ethio zurik swizerlabd sport spokesperson የዙሪክ ስዊዘርላንድ ኢትዮጵያውያን ስፖርት ማሕበር (ፌዴሬሽን) አመራር አባል አንዱ ቴድሮስ ተክለግዮርግስ የፌደሬሽኑ ቃል አቀባይ።

**መግቢያ :**

ይህ ሰነድ ለብዙዎቹ የተቃዋሚ ድረገጾች ልኬአለሁ። አንዳንዶቻችሁ ለምን ይተቸናል ብላችሁ ከዚህ ጸሐፊ ጋር ያላችሁ ለተለመደው የፖለቲካ አለመስማማት ስትሉ “ቂምን እያፕካችሁ” ይህንን ታላቅ ታሪካዊ ስራ ለሕዝብ እንዳይዳረስ በድረገጾቻችሁ ላለማውጣት ስትሉ እንደዘወትሩ ወደ ቆሻሻ መጣያችሁ ብትጥሉት፤ እኔን ሳይሆን የነዚህ አርበኞች ስራ እና ታሪክ እንደጣላችሁ ስለሚቆጠር፤“ወደ ኋሊት” እየተነተተ ያለው ወገናዊ የሚዲያ አገልግሎታችሁን

ወደ ጎን አኑሩትና" ይህንን ሰነድ በድረገጾቻችሁ ብትለጥፉት ብዙ ዜጎችን ስለሚያስተምር እናንተም ከአድሎአዊ ስራ ከመወቀስ 'ነጻ' ከማድረግ አልፎ፤ ጋዜጠኝነት የምትሉትን ሞያችሁን ያስመሰግናል እንጂ በታሪክ አያስወቅሳችሁም። ይህ ሰነድ የተላከላቸው ድረገጾች ያወጡት መሆናቸው እና አለመሆናቸው ሕዝቡ እንድያገናዝበው አድራሻቸው ከወደ መጨረሻው ይታያል። አድራሻችሁን ያላገኘሁ ካለሁ፤ ከተለጠፉት ድረገጾች በማግኘት መለጠፍ ትችላላችሁ።

በታላቁ ኢትዮጵያዊው ዮፍታሄ ንጉሤ የተነገረ እውነታ ልጀምር፡

"አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ ያልሞተልሽ በላ"። ለኢትዮጵያ አንድነት ፤ ብልጽግና ክብርና ነፃነት ሲሉ በቃላት ለመግለጽ በሚከብድ ከፍተኛ መስዋእት እና በጎ ስራ ሰርተው ያለፉ በርካታ ዜጎቿ ያለ አስታዋሽ ሳይታወቁ የትም ወድቀው ቀርተዋል። በህይወት የሚገኙ እራሳቸውም ሆነ ቤተሰቦቻቸው ያሉበትን ህይወት ፈትሸን ለማየት ትኩረት አላደረግንም። ብዙዎቹ ብቻ ሳይሆኑ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ለከፋ ህይወት ተጋልጠው በድህነትና በበሽታ ተጠቅተው በቁጭት፤ በልቅሶ፤ በትዝታ እና በበሽታ እየተሰቃዩ መሆናቸውን "መንግሥት" "ተብየውም" ሆነ እኛ እንደ ዜጎች ያደረግነው ፍተሻ እንደሌለ ይህ ሰነድ ማስረጃ ነው።




Yosef Gebre with the Welaita Artis Kosha Seta ታዋቂው የወላይታ ድምጻዊ ኮሻ ሴታ በአሳዛኝ የድህነት ኑሮ

በጦር ሜዳ የተካፈሉ፤ የተሰው ጀግኖች አርበኞች፤በጋዜጠኛነት፤በከያኒነት የታወቁ ብዙ አስተዋጽኦ ያደረጉ ዜጎች፤ ቤተሰቦቻቸውም ሆነ እራሳቸው ዛሬ ያሉበት ኑሮ ፈትሾ ለተከታታይ አመታት የገና በዓል በመጣ ቁጥር በቴ/ቪዥን ለሕዝብ እያሳየ ያለው የኪነት ሰው ታላቁ ወጣት ኢትዮጵያዊ ዮሴፍ ገብሬ (ጆሲ ኢን ዘ ሓውስ ሾው) የእያንዳንዳችንን ሕሊና እንድንፈትሽ የወጠረን ታላቅ ወጣት ኢትዮጵያዊ፡ እኔ ጌታቸው ረዳ እንደ የትግርኛና አማርኛ መጽሐፍት ደራሲ እና ተቺ፤ እንዲሁም

እንደ የኢትዮጵያ ሰማይ ድረገጽ (Ethiopian Semay) አዘጋጅነቴ ይህ ታላቅ ወጣት በመላው ዓለም ያሉ ዜጎች በክብር መዝገባቸው እንድያስታውሱት፤ እንዲሁም ‘የታሪክ ዘጋቢዎች’ ካሉንም (እንደሌሉን ስለማውቅ ነው፡ ስለ የታሪክ እና የሕግ ምሁራን ‘ተብየዎቻችን” ካሁን በፊት ብዙ ስለጻፍኩ አሁን አልመለስበትም። አንዳንዶቹን ግን ሳላመሰግናቸው አላልፍም) እንዲዘግቡት መልእክቴን አስተላልፋለሁ።



Belay Zeleke daughter YeShash Werk Belay's grand children Genete and her brtother እነዚህ በፎቶ ላይ የሚታዩ ሁለት ይናማዎች የበላይ ዘለቀ የልጅ ልጆች ወ/ሮ ገነት እና የወ/ሮ ገነት ወንድም ፎቶግራፍ ነው። መንግሥት መኖሪያቸው እና እናታቸው የተውላቸውን የተከራይዋትን ትንሽ የንግድ ግሮሶሪ ዘግቶባቸው ሦስተኛው ወንድማቸው በአእምሮ በሽታ ተለክፎ ሲሰቃይ እንኚህ የተቀሩትም ለድህነትና ለመራራ ብስጭት ተዳርገዋል። (ይህች አገር ምን ብናደርግ ይሻላት ይሆን !? የሚለው ጥያቄ የሁላችን ጥያቄ እንደሆነ ተሰፋ አለኝ።)

ከዚህም ጋር አብረው ከዮሴፍ ገብሬ ጋር ቀኝ እጁ ሆኖው በርካታ የገንዘብ እና የሞራል ድጋፍ ለነዚህ ባለውለታዎቻችን እና ቤተሰቦቻቸው የሚለግሱትን አገር ውስጥ ያሉ በጎ አድራጊ ግለሰቦች እና የንግድ ተቋማት ምስጋና እያቀረብኩ፤ በተለይም ደግሞ በጎላ ዓይን አትኩሮታችሁ እንድትሰጡት የምፈልገው እዚህ እኛ ጋር እውጭ አገር አውሮጳ ያለ ተቋም አለ። ይኸውም የዙሪክ ኢትዮጵያውያን ስፖርት ማሕበር (ፌደረሽን)” በመባል የሚታወቅ “ዙሪክ (ኔዘርላንድ) የሚገኝ ታላቅ የእስፖርት ማሕበር አመራሮች እና በጎ አድራጊዎቹ ከዮሴፍ (ጆሲ ኢን ዘ ሓውስ) ጋር ሆነው በመነጋጋር ከአባላቱ ያሰባሰቡትን ገንዘብ ለነዚህ ባለውለታዎቻችን እና ቤተሶቦቻቸው ቃላት በሚያጥረኝ ሁኔታ እያደረጉት ያለውን ዜጋዊ የተቀደሰ የዕርዳታ ተግባር ለዚህ ተቋም አስተባባሪዎች እና አባሎች ያለንን አክብሮት እንድንግልጽ ለመላ ኢትዮጵያዉያን ጥሪ አቀርባለሁ። በበኩሌ በሚቀጥለው መጽሐፌ ውስጥ ለነዚህ በጎ አድራጊ ምርጥ ኢትዮጵያውያን ታሪክ እንዲዘግባቸው ራሱን የቻለ ምዕራፍ ለግሼ ስለ በጎ ተግባራቸው ከነፎቶግራፋቸው እገልጻለሁ።



Gizachew Amakele on sick bed  interviewed by  Josy in the house በዮሴፍ ገብሬ (ጆሲ) በገና በዓል የተጎበኘ እና በዙሪክ አውሮጳ ስፖርት ፌዴረሽን የገንዘብ ዕርዳታ የተደረገለት ታዋቂው ሙዚቀኛ ግዛቸው አማከለ እግሮቹ አላላውስ ብሎት የአልጋ ቁራኛ ከሆነ 5 አመቱ።





Gezachew Amakele  before time betrayed him ግዛቸው አማከለ ጊዜ ሳይከዳው በጎልማሳ ጤንነት ጊዜ

የአፄ ምኒልክ አንበሳ ከጫካ እየነዱ ለንጉሡ ካስረከቡዋቸው መካከል የንጉሡ አገልጋይ የነበሩት በረዢም ዕድሜአቸው የታወቁ፤ በተዘጋች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ ብቻቸውን በመኖር 'ዓይነ ስውር' ሆነው በድህነት የኖሩ፤ መንግሥት የረሳቸው፤ነገር ግን እኝያ ታሪካዊ ዜጋ በማስታወስ፤ በውጭ አገር የሚኖር የአንድ ታዋቂ ጀኔረል ልጅ ሲረድዋቸው የነበሩት (ዛሬ ይኑሩ ይሙቱ አላወቅኩም፤ እስከ

ቅርብ አመታት ጊዜ ግን ነበሩ) ፤ እና እንዲሁም የነ ልጅ እያሱ ልጆች/የልጅ ልጆች/፤ እና የእነ በላይ ዘለቀ የልጅ ልጆች፤ የነ ሃይለማርያም ማሞ ልጆች (ሃይለማርያም ማሞ የጦሩ ገበሬ፤ ፈረሱን እንደሰው አስታጠቀው ሱሬ!!) የተባለላቸው ቤተሰቦች አልባሌ ቦታ የትም ወድቀው ሲቀሩ፤ የሚበሉት የሚጠጡት አጥተው አስታዋሽ ሲያጡ፤ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች "ዮሴፍ ገብሬ እና የዙሪክ ኢትዮጵያውያን ስፖርት ማሕበር (ፌደረሽን)" ከሚሰቃዩበት የድህነት ኑሮ ፤ ከወደቁበት ቦታ ድረስ ሄደው ሲረዷቸው "መንግሥት ተብየው" ግን ረስቶአቸው ለኢትዮጵያ አርበኞችና ባለሞያዎች ያለውን ጥላቻ በግልጽ እንድናየው አድርጎናል። ያውም ከሚኖሩበት እና የነበራቸውን አነስተኛ የንግድ ሱቅ "በአረመኔ የቀበሌ ተላላኪዎቹ" በኩል እየዘጋና እያፈናቀለ! (አሳዛኝ ታሪካቸውን ከታች ባያያዝኩዋቸው የቪድዮ ሰነዶች ትመለከቱታላችሁ።)




Hailemariam Mamo's daughter Zenebech Hailemariam ጣሊያንን ድባቅ የመቱት ታዋቂው አርበኛ የጦሩ ገበሬ የተባለላቸው የአርበኛው ሃይለማርያም ማሞ ልጅ እራሳቸውም በጦር አርበኛነትና በፉከራ የታወቁት ወ/ሮ ዘነበች ሃይለማርያም ለነብሴ ብለው ባስጠግዋቸው ዜጎች እጅ ወድቀው በሚያሳቅቅ ኑሮ ሲኖሩ ዮሴፍ ገብሬ (ጆሲ) ሲያነጋግራቸው። (የኢትዮጵያ የዙሪክ የስፖርት ማሕበር ታላቅ ስራ በመስራት ላይ ያለውን ተሳትፎ በሁሉም ሰነዶች ከታች እንመለከተዋለን)

እነዚህ ምርጥ ኢትዮጵያውያን እያደረጉት ያለው በዓይነቱ ለየት ያለ ተግባር ለማየት "በዩ-ትዩብ" የተለጠፉትን ቪዲዮዎች እንድትመለከትዋቸው ከታች ተያይዘዋል። ያንን ስትመለከቱ ልብ የሚሰብሩ በእምባ የታጀቡ አሳዛኝ ታሪኮች ስለምታደምጡ የልብ በሽታ ወይንም የደም ግፊት... ካላችሁ ረጋ ብላችሁ በጥንቃቄ ተመለከቱት። የሚያስለቅስ ያህል የሚያስደስትም ስላለበት ሁሉንም በየመልኩ ተመልከቱና "መንግሥት" ማለት ጸረ ሕዝብ የሚሆንበት ሁኔታ እንዳለ በነዚህ ሰነዶች (ጆሲ በሚያሳየን አሳዛኝ ፕሮግራም) እናያለን ።







የፖሊስ ሰራዊት ድምጻዊት ወይንሸት ሙሉነህ (በስልክ አነጋግረኝ በቀጭኑ ሽቦ የሚለውን ዘፈን ከታደለ በቀለ ጋር አብራ የምትዘይመው ጣዕመኛዋ ድምጻዊት ዕርዳታ ሲደረግላት የታየው አሳዛኝ ፤አስለቃሽ ኑሮ እና መጨረሻ በነዚህ ታላቅ የዓመቱ ሰዎች እና አገር ውስጥም ያሉት በጎ አድራጊዎች ዕርዳታ በደስታ የተደመደመው ህልም በሚመስል ግን ወደ እውነታ የተቀየረው የድምጻዊት ወይንሸት ሙሉነህ ህይወት በቪድዮው ውስጥ ትመለከቱታላችሁ)

መንግሥት የሚባለው "አረመኔ አራዊት" ምን ማለት ነው? የሚለውን ግራ እንዳይገባችሁ ከጻፍኩት ከአዲስ መጽሐፌ ከፈላስፋው ፍሬዴሪክ ኒቼ ገለጻ ልጥቀስ፡-

‘እኛ መንግሥት ነን፤ መንግሥት ማለት ሕዝብ ማለት ነው ይላሉ መንግሥታቶች….። ይላል ፈላስፋው ፍሬዴሪክ ኒቼ። በመቀጠልም “መንግሥት የከፉዎቹ ሁሉ ከፉ አውሬ ነው።” ይለናል። መንግሥት በሁሉም ቋንቋዎች የሚዋሽ አፍ ነው። መንግሥት የተፈጠረው ለኒህ እልፍ አእላፍ ሰዎች ነው። ይህ መንግሥት የሚባለው፤ ሕዝቦቹን እንዴት እንዴት እንደሚያባብላቸው ብቻ ተመልከቱልኝ። ሲያላምጣቸው፤ መልሶ መላልሶ ሲያኝካቸው አያችሁልኝ?“ ይላል ‘ኒቼ’። አዎን በአውሬዎች መሃል ተከብበን እያላመጡ መልሰው መላልሰው አኝከውናል….። ይላል ኒቼ። “ኒቼ” መንግሥት ሲሞት ቀስተዳመና ይወለዳል’ ይላል። ኢትዮጵያም በቀስተዳመና መቀነትዋ ዙርያ ብቅ ብላ እንደጥንቱ ሰንደቃላማዋን ይዛ የዚህ ስርዓት ሞት ታበስራለች። አንድ ቀን! ” ከራሴው መጽሐፍ መግቢያ የተወሰደ።





Actor Jembere Belay ተዋናይ ጋሽ ጀምበሬ በላይ በመድረክ ትወና ወቅት የተነሳው ፎተግራፍ

የሴፍ ገብሬ (ጆሲ ኢን ዘ ሃውስ ሾው) ባዘጋጀው የገና በዓል ዝግጅት ብዙዎቹ የአርበኞች ልጆችና ባለሞያዎች ቤት አጥተው የትም ተጥለው ታያላችሁ። መንግሥት ተብየውም ሲታመሙ ሊያሳክማቸው አልቻለም።ከሚዘርፈው የአገሪቱ ሃብት ትንሽም ብትሆን ‘ሲጠሙ ሲታረዙ’ ሊረዳቸው አልፈለገም። የሚኖሩበት እና የሚሰሩበት ንግድ ቤቶቻቸውን ዘግቶ ለመከራ አጋልጦአቸዋል። ከብዙ አመታት በፊት እነ “ሉቺያና ሳንቲያኖ ባሳሎ” ምርጥ ብሔራዊ እግር ኳስ ተጫዋቾቻችንን ኢትዮጵያ ውስጥ የገነቡት ቤቶቻቸውን ወያነ የተባለ መንግሥት ‘ኢሳት’ በተባለው ‘ቴ/ቪዥን’ ባደረገላቸው ቃለ መጠይቅ እንዴት እንደነጠቃቸው ያደመጣችሁ እንዳላችሁ አምናለሁ። እነኚህን የመሳሰሉ ባለውለታዎች፤ አርበኞች እና የአርበኞች የልጅ ልጆች ህይወትና መስዋእትነት በመዘንጋት ‘መንግሥት እያሉ ራሳቸውን የሚጠሩ’ መንግሥቶች ሃላፊነታቸው ለምን እንደሚዘነጉ እነዚህን አርበኞችና ቤተሰቦቻቸውን በሚመለከት በሚቀጥለው መጽሐፌ በሰፊው የምገለጸው ይሆናል። አሁን ያለው ጥያቄ ግን ‘ኢትዮጵያ የሞቱላትንና የደከሙላትን ልጆቿን መርሰትዋን እስከመቸ እንዲህ እንዲቀጥል እንፈቅዳለን?’።

እነኚህ የ2018 የአመቱ ሁለት ምርጥ ኢትዮጵያውያን ዮሴፍ ገብሬ (ጆሲ- ኢን ዘ ሃውስ) እና የዙሪክ ኢትዮጵያውያን እስፖርት ፌደረሽን የ2018 የፈረንጅ አመት ምርጥ ዜጎች በያለንበት ዓለም ከተቀመጥንበት ተነስተን በተረዱት ወገኖቻችን ስም በአክብሮት እንስገድላቸው። ጊዜ መድባችሁ፤ ከታች ያሉት የቪዲዮ ሰነዶችን ማየት እንዳትረሱ።

ኢትዮጵያ የሞቱላትን እንጂ የገደልዋትን ማገልገልዋን ታቁም!

እግዚአብሔር ውለታችሁን ይክፈላችሁ። አሜን!

ጌታቸው ረዳ ዘብሔረ አክሱም (Author and Editor Ethiopian Semay)

getachre@aol.com

jossy show ልዩ የበአል ፕሮግራም በጆሲ ሾው

**https://youtu.be/ky_TnMy-nh0**

**Jossy in Z House Show - Ethiopian Christmas Special 2007**

https://youtu.be/4VI4K_Lq30Y

**jossy show ልዩ የበአል ፕሮግራም በጆሲ ሾው**

https://youtu.be/85tm1GWk74c